

## መልክዐ አቡነ ብፁዐ አምላክ (ዘአኀተሞ ገብረ ሥላሴ)

| መልክዐ አቡነ ብፁዐ አምላክ-ግዕዝ | የአቡነ ብፁዐ አምላክ መልክዕ በአማርኛ |
| --- | --- |
| ፩. ሰላም ለዝክረ ስምከ በሠሌዳ ሞገስ ዘተቀልመ፤ ወበጼወ ክህነት ተቀሥመ፤ ብፁዐ አምላክ ዐዋዲ አንተ ሰበከ ዓለመ፤ እንዘ ትብል ወልደ አምላክ በእንተ ፍቅረ ሰብእ ዘሐመ፤ በከመ ዳዊት ነበበ ወቄርሎስ ተርጐመ፡፡ | 1. ለዝክረ ስምከ፡- ዳዊት እንደተናገረ ቄርሎስም እንደተረጐመ ወልደ አምላክ ስለ ሰው ፍቅር ታመመ እያልህ ዓለምን የምትሰብክ ዐዋጅ ነጋሪ ብፁዐ አምላክ ሆይ! በግርማ ሞገስ ብራና ተጽፎ በክህነት ጨው ለተቀመመው ስም አጠራርህ ሰላምታ ይገባል፡፡ |
| ፪. ሰላም ለሥዕርተ ርእስከ እለ መነና ምናኔ፤ ተፀፍሮ ቈናዝል ወቅብዐ ግማኔ፤ ብፁዐ አምላክ ብልጣሶር አብሣሬ ግዕዛን እምግብረ ቅኔ፤ ዘልፎሙ ለአፅራርየ በብሂለ ቴቄል ወማኔ፤ ወእንግልጋሆሙ ረሲ ዘኀሣር ዅርጓኔ፡፡ | 2. ለሥርዕተ ርእስከ፡- ከባርነት ሥራ ነፃነትን የምታበሥር ብፁዐ አምላክ ዳንኤል ሆይ! ጠጕር ማሳደግን የኀጢአት ቅባትንም ለናቀ ለራስህ ጠጕር ሰለምታ ይገባል፤ ጠላቶቼንም ‹ማኔ ቴቄል› በማለት አዋርዳቸው፤ ጉባኤያቸውንም የውርደት ጉባኤ አድርግባቸው፡፡ |
| ፫. ሰላም ለርእስከ ዘኑባሬሃ አዳም፤ አምሳለ ማኅቶት ዘወርቅ ዲበ ሥጋከ ተቀዋም፤ ብፁዐ አምላክ ባዕል ለዐሳብከ ድኩም፤ ደሊወከ በዲድርክም፤ ምስለ እለ ጻመዉ እምቅድም፤ ዲናረ ዐስበ ጽድቅ ሀበኒ በሐዳስ ዓለም፡፡ | 3. ለርእስከ፡- በሥጋህ መቅረዝ ላይ በወርቅ መብራት አምሳል ለተቀመጠች ራስህ ሰላምታ ይገባል፤ ባለጸጋ ብፁዐ አምላክ ሆይ! ደካማ አገልጋይህን እኔን ከፊት ከደከሙት ጋራ በዲድርክም መዝነህ የጽድቅ ዋጋ ገንዘብን በዐዲስ ዓለም ሰጠኝ፡፡ |
| ፬. ሰላም ለገጽከ ከመ ገጸ ያዕቆብ ዕሥራኤል፤ ዘአፍቀረ ሥኖ እግዚአብሔር ልዑል፤ ብፁዐ አምላክ ጌዴዎን ያርብሓዊ ኀያል፤ ባርከነ ለደቂቅከ በበረከተ እድ ወቃል፤ ወፀምረ ሰብእናነ አርዊ በፍቅርከ ጠል፡፡ | 4. ለገጽከ፡- ኀያል ጕበዝ የሆንህ ብፁዐ አምላክ ጌዴዎን ሆይ! ልዑል እግዚአብሔር ውበቱን እንደ ዕሥራኤል ያዕቆብ ለወደደው ፊትህ ሰላምታ ይገባል፤ ልጆችህን በእጅና በቃል በረከት ባርከን፤ የሰውነታችንን ግምጃም በፍቅር ጠል አረስርሰው፡፡ |
| ፭. ሰላም ለቀራንብቲከ እምንዋመ ሀኬት እለ ጽሒዋ፤ ምጽአተ መርዓዊ ክርስቶስ እንዘ ይሴፈዋ፤ ብፁዐ አምላክ ለጥበብ ዘሠረፅከ እምነ ሥርዋ፤ ኢተሰምዐ ከመ ከማከ እምደቂቀ አዳም ወሔዋ፤ ምህርካ ነፍሳት እምሲኦል ዘአዕረገ ጼዋ፡፡ | 5. ለቀራንብቲከ፡- ከጥበብ ሥር የበቀልህ ብፁዐ አምላክ ሆይ! የሙሽራው ክርስቶስ መምጣትን ተስፋ አድርገው የስንፍና እንቅልፍ ለአላገኛቸው ቅንድቦችህ ሰላምታ ይገባል፤ ከአዳምና ከሔዋን ልጆችም እንደ አንተ ያለ ነፍሳትን ከሲኦል ምርኮ አድርጎ ያወጣ አልተሰማም፡፡ |
| ፮. ሰላም ለአዕይንቲከ ዘኢያፍትዎን ተነሶሕሎ፤ እምእብነ ሐሰት ምድራዊ ዘያመጽእ ግብረ ተንኰሎ፤ ብፁዐ አምላክ | 6. ለአዕይንቲከ፡- የምድረ ሴሎ ነቢይ የሆንህ ብፁዐ አምላክ ሳሙኤል ሆይ! የጥፋት ሥራን ከሚያመጣ ከሐሰት ደንጊያ መካከል መኳል ለአላስጐመጃቸው |

| | |
|---|---|
| ሳሙኤል ነቢይ ዘምድረ ሴሎ፣ ጸሎትከ ሰይፈ መዊዕ ወኲናትከ ተንብሎ፣ ለፍትወተ ዓለም ኢጋግ እስከ ዮም ቀተሎ፡፡ | ዐይኖችህ ሰላምታ ይገባል፤ የማሸነፍ ሰይፍ ጸሎትህና አማላጅነትህ ጦርህም የዓለም ምኞት አጋንንትን እስከ ዛሬ ድረስ ይግደለው፡፡ |
| ፯.ሰላም ለአእዛኒከ ቃላተ ሥላሴ እለ ሰምዓ፤ ወትእዛዞሙ አጽንዐ፤ ብፁዐ አምላክ ዕንባቆም ዘፍና ተልእኮ አርትዐ፤ ለዳንኤል ሰብእናየ ውስተ ግበ ዓለም ዘቦአ፤ ሲሳየ መድኀኒት እምጽእ ወዘጽድቅ መብልዐ፡፡ | 7. ለአእዛኒከ፡- የመላላክ ጐዳናን የአቀናህ ብፁዐ አምላክ ዕንባቆም ሆይ! የሥላሴን ቃላት ሰምተው ትእዛዛቸውን ለአጸኑ ጆሮዎችህ ሰላምታ ይገባል፤ ወደ ዓለም ገደል ለገባ ለዳንኤል ሰውነቴም የድኅነት ምግብንና የጽድቅ መብልን አምጣለት፡፡ |
| ፰.ሰላም ለመላትሒትከ እለ አብዝኀ ተጸፍዖ፤ እንበይነ ጽፍዐቱ ለወልድ ዘፈጸመ ግብረ ተሰብኦ፤ ብፁዐ አምላክ ናዖድ እስመ ብከ ግብረ ተበፅዖ፤ ለኤግሎም ፀረ ነፍስየ ኀይለ ዚአከ ይጽብዖ፤ መጥባሕተ መድኀኒት ቅንት ወተንሥእ እግዚኦ፡፡ | 8. ለመላትሒከ፡- ብፁዐ አምላክ ናዖድ ሆይ! ሰው የመሆን ሥራን ስለፈጸመ ስለ እግዚአብሔር ወልድ መጸፋት መመታትን ለአበዙ ጕንጮችህ ሰላምታ ይገባል፤ የመደነቅ ሥራ አለህና ኤግሎም ጠላቴን በአንተ ኀይል ያሸንፈው ዘንድ የመድኀኒት ሰይፍን ታጥቀህ አቤቱ ተነሥ፡፡ |
| ፱. ሰላም ለአእናፊከ አጼንዎ እለ መነና፤ መዐዛ ፈዋት ዘአንስት ዘያመጽእ ግብረ ሙስና፤ ብፁዐ አምላክ ሙሴ ትምክሕተ ደቂቃ ለዲና፤ በደብርከ ደብረ ምስካይ ካልእተ ድብረ ሕግ ሲና፤ ለሲሳየ ሕዝብከ አውርድ እክለ ጽድቅ መና፡፡ | 9. ለአእናፍከ፡- የዲና ልጆች መመኪያ የሆንህ ሙሴ ብፁዐ አምላክ ሆይ! የጥፋት ሥራን የሚያመጣውን የሴቶች ሽቱን ማሽተትን ለናቁ አፍንጫዎችህ ሰላምታ ይገባል፤ የሕግ ተራራ ለሆነች ለሲና ኹለተኛ ለሆነች በደብረ ምስካይ ደብርህም ለወገኖችህ ቀለብ የሚሆን የጽድቅ እህል መናን አውርድ፡፡ |
| ፲. ሰላም ለከናፍሪከ ስብሓተ ሥላሴ እለ አውኀዛ፤ እምአፉከ ነቅዐ መዐዛ፤ ወላዴ ዕሥራኤል አእላፍ ብፁዐ አምላክ ወሬዛ፤ እንዘ ይተክሉ ሰዋስወ ኪዳን ወቤዛ፤ ኢጋዕዝተ ሰማይ ወረዱ በቤትከ ሎዛ፡፡ | 10. ለከናፍሪከ፡- የብዙ ዕሥራኤል ወላጅ ብፁዐ አምላክ ያዕቆብ ሆይ! የጥሩ መዐዛ ምንጭ ከሆነ አፍህ የሥላሴን ምስጋና ለሚያፈስሱ ከንፈሮችህ ሰላምታ ይገባል፤ የሰማይ ጌቶችህ ሥላሴ የቃል ኪዳን እና የድኅነት መሰላል ተክለው በቤትህ ሎዛ ወረዱልህ፡፡ |
| ፲፩. ሰላም ለአፉከ አንቀጸ ሠናይ ንባብ፤ ወሙፃአ ነገር ቅዱስ እመዝገበ ንጹሕ ልብ፤ ብፁዐ አምላክ ዳንኤል ዘአልሐቀተከ ጥበብ፤ አመ ቦእከ ለተጋድሎ ውስተ ቤተ ጸሎት ግብ፤ ለሐውጾትከ መጽአ ዕንባቆም ኪሩብ፡፡ | 11. ለአፉከ፡- ጥበብ የአሳደገችህ ዳንኤል ብፁዐ አምላክ ሆይ! የመልካም ነገር በርና ከንጹሕ የልብ መዝገብ የቅዱስ ነገር መውጫ ለሆነ አፍህ ሰላምታ ይገባል፤ ለመገደልም ወደ ጸሎት ቤት ገደል በገባህ ጊዜ ለመጕብኘት ዕንባቆም ኪሩብ መጣልህ፡፡ |
| ፲፪. ሰላም ለአስናኒከ ዘጽዕዳዊሆን ነከራ፤ ለጽዕዳዌ በረድ እምነ ኀብራ፤ ብፁዐ አምላክ ኢዮብ ለትዕግሥት ሕንጻ ማኅደራ፤ ህየንተ | 12. ለአስናኒከ፡- ለትዕግሥት ቤቷ የሆንህ ብፁዐ አምላክ ኢዮብ ሆይ! ከበረድ ንጻት ኀብር ይልቅ መንፈስ ቅዱስ ንጻት ለሆናላቸው ጥርሶችህ ሰላምታ ይገባል፤ መከራን |

| | |
|---|---|
| ዘፆርከ ወተዐገሥከ መከራ፤ መልአከ ሰማይ በክንፍ ለነፍስከ ጾራ፡፡ | ታግሠህ ስለተሸከምህ የሰማይ መልአክ ነፍስህን በክንፍ ተሸከማት፡፡ |
| ፲፫. ሰላም ለልሳንከ ዘይነብብ ጽድቀ፤ ወነገረ ጥበብ ጥዩቀ፤ ብፁዐ አምላክ ሀበኒ አንብዐ ንስሓ ጽፉቀ፤ በሀኬተ ወበንዝኅላል እስመ ዘመንየ ኀልቀ፤ ወኮንኩ ከመ ጽጌ እምዐፅቁ ዘወድቀ፡፡ | 13. ለልሳንከ፡- ብፁዐ አምላክ ሆይ! እውነትንና የጐላ የጥበብ ነገርን ለሚናገር አንደበትህ ሰላምታ ይገባል፤ ብዙ የንስሓ ዕንባንም ስጠኝ፤ በስንፍና በዙረት ዘመኔ አልቋልና ከግንዱ ተለይቶ እንደ ወደቀ አበባም ሁኛለሁና፡፡ |
| ፲፬. ሰላም ለቃልከ ከመ ድምፀ ናብሊስ ተጸንጻሊ፤ ዕፀበ ሕማም መርስዒ ወከበደ ኀዘን መቅለሊ፤ ብፁዐ አምላክ ወትረ አድኅኖተ ነፍስየ ሐሊ፤ ወብትክ እምላዕሌየ ማእሰረ ሰይጣን ቀታሊ፤ እስመ ሥልጣኖሙ ብከ ለጴጥሮስ ወለጳውሊ፡፡ | 14. ለቃልከ፡- ብፁዐ አምላክ ሆይ! እንደ አታሞ ድምፅ በሚንሿሻና የሕማም ጭንቅን ለሚያስረሳና የኀዘን ሸክምን ለሚያቀል ቃልህ ሰላምታ ይገባል፤ ብፁዐ አምላክ ሆይ! የጴጥሮስና የጳውሎስ ሥልጣን አለህና ነፍሴን ለማዳን ዘወትር አስበኝ፤ የነፍሰ ገዳይ የሰይጣንንም ማሰሪያ ከእኔ ላይ ቍረጥ፡፡ |
| ፲፭. ሰላም ለእስትንፋስከ በነፌሖቱ ዘአቍረራ፤ ለሲኦል ግበ መከራ፤ ብፁዐ አምላክ ኤርምያስ ወነቢየ አርፋድ ዕዝራ፤ ለጽዮን ቤተ ነፍስየ ከመ ይትሐነፅ ማኅደራ፤ ሰቆቃወ ጸሎት ላዕሌሃ ኢታንትግ ለግሙራ፡፡ | 15. ለእስትንፋስከ፡- የአርፋድ ነቢይ ዕዝራንና ኤርምያስን የሆንህ ብፁዐ አምላክ ሆይ! የመከራ ገደል ሲኦልን እፍ በማለት ለአቀዘቀዛት እስትንፋስህ ሰላምታ ይገባል፤ ለነፍሴ መግቢያ የጽዮን ቤቷ ይሠራ ዘንድ የልቅሶ ጸሎትን ከላየ ላይ ፈጽመህ አታስታጉል፡፡ |
| ፲፮. ሰላም ለጕርዔከ ወይነ መንፈስ ቅዱስ ዘአርወዮ፤ እሳተ ፍቅሩ ለወልድ ሰበ አውዓዮ፤ ብፁዐ አምላክ ኀያል ድርዐ ሃይማኖት በተረስዮ፤ መዛግብተ ሲኦል ሶበ ሐብለይከ ሐብልዮ፤ መኰንነ ጽልመት ደንገፀ ኀይለከ ርእዮ፡፡ | 16. ለጕርዔከ፡- ብርቱ ብፁዐ አምላክ ሆይ! የእግዚአብሔር ወልድ የፍቅሩ እሳት በአቃጠለው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወይን ለአረካው ጕሮሮህ ሰላምታ ይገባል፤ የሃይማኖት የጦር ልብስንም በመልበስ የሲኦል መዛግብትን መበርበርን በበረበርህ ጊዜ የጨለማው ገዥ ኀይልህን አይቶ ደነገጠ፡፡ |
| ፲፯. ሰላም ለከሣድከ ህየንተ ባዝግና ዘወርቅ፤ አስኬማ መላእክት ዘኮኖ ወርቀ ቅድስና ወጽድቅ፤ ብፁዐ አምላክ በርሱማ እምንዋየ ዓለም ዕሩቅ፤ እፎ ፈጸምከ ተጋድሎ ውስተ ውሳጤ ግብ ዕሙቅ፤ ኀበ ብርሃነ ወርኅ አልቦ ወፀሐይ ምውቅ፡፡ | 17. ለከሣድከ፡- ከዓለም ገንዘብ የራቅህ ብፁዐ አምላክ በርሱማ ሆይ! ስለ ወርቅ ማርዳ ፈንታ የመላእክት አስኬማ የቅድስናና የጽድቅ ወርቅ ለሆነለት አንገትህ ሰላምታ ይገባል፤ የጨረቃና የፀሐይ ብርሃን በሌለበት በጥልቅ ገደል ውስጥ ተጋድሎን እንዴት ፈጸምህ! |
| ፲፰. ሰላም ለመታከፍቲከ በአርዑተ ጥበብ ጽሙዳን፤ ወበመንፈሰ ኀይል ከቡዳን፤ ብፁዐ አምላክ ሶምሶን መልአከ ኀይሉ ለዳን፤ | 18. ለመታከፍቲከ፡- የዳን የነገዱ አለቃ የሆንህ ብፁዐ አምላክ ሳምሶን ሆይ! በጥበብ ቀንበር ለተጠመዱና በኀይል መንፈስ ለጸኑ ትከሻዎችህ ሰላምታ ይገባል፤ የአጋንንት ውኃ ማኅበርተኞች የሆኑ ጠላቶቹ |

| | |
|---|---|
| ይትቀጥቀጡ በመዝራዕትከ ወበኀይልከ እጥናን፤ ማኅበረ ኢጋንንት ፀርየ ኢሎፍሊ አብዳን፡፡ | ኢሊፍላውያንም በክንድህና በጠንካራ ኀይልህ ይቀጥቀጡ፡፡ |
| ፲፱. ሰላም ለዘባንከ መንበረ ስብሓት ዘውገ ኪሩብ፤ ወምዕራፈ ኀሪት ጥበብ፤ ብፁዐ አምላክ እሴር እከለ በረከት ጽጉብ፤ ሴስየኒ እከለ ቤትከ ወኢትበለኒ እብ፤ ውሂበ ኀብስት ለውሉድ ኢመፍትው ለከልብ፡፡ | 19. ለዘባንከ፡- የበረከት እህልን የጠገብህ ብፁዐ አምላክ አሴር ሆይ! ኪሩብ በሚወግንበት ምስጋናና ለተመረጠች ጥበብ ማረፊያ ለሆነ ጀርባህ ሰላምታ ይገባል፤ የቤትህን እህል መግበኝ እንጂ አባት ሆይ! የልጆችን እንጀራ ለውሻ መስጠት አግባብ አይደለም አትበለኝ፡፡ |
| ፳. ሰላም ለእንግድዓከ እንተ የዐውዶ ሞገስ፤ ከመ እንግድዓሁ ለዕዝራ ስኩረ መንፈስ፤ ብፁዐ አምላክ ዮሐንስ ተሐራሜ ወይን ወሜስ፤ ከመ ይድኀን ወይን እምበረድ ወእምአስሐትያ በለስ፤ ባርክ ዐውደ ዓመት ወዕተብ ቀሲስ፡፡ | 20. ለእንግድዓከ፡- ከወይንና ከጠጅ የተከለከልህ ብፁዐ አምላክ ዮሐንስ ሆይ! በመንፈስ ቅዱስ እንደ ሰከረ እንደ ዕዝራ ደረት ሞገስ ለከበበው ደረትህ ሰላምታ ይገባል፤ ቀሲስ ሆይ! ከበረዶ በለሱ ከወርጭ ይድን ዘንድ ዐውደ ዓመቱን ባርክልን፡፡ |
| ፳፩. ሰላም ለሕፅንከ ከላስስተ ትዕግሥት ወገድል፤ እንተ አስተጋባእከ ቦቱ እምገራህተ ቅዱስ ወንጌል፤ ብፁዐ አምላክ ወሬዛ ምሁረ ፀብዕ ወቀትል፤ ዜዊወከ ዜዋ አመ ዐረገ በኀይል፤ ደናግለ ሰማይ የበባ በዐቢይ ቃል፡፡ | 21. ለሕፅንከ፡- ሰልፍንና ጦርነትን የተማርህ ብፁዐ አምላክ ጐበዝ ሆይ! ከቅዱስ ወንጌል እርሻ የትዕግሥትና የገድል ነዶዎችን ለሰበሰብህበት እቅፍህ ሰላምታ ይገባል፤ ምርኮንም ማርከህ በወጣህ ጊዜ የሰማይ ደናግል በታላቅ ቃል እልል አሉ፡፡ |
| ፳፪. ሰላም ለአእዳዊከ ለስኢለ ምሕረት እምኀበ አብ፤ እለ ስፋሓት እማንቱ በአርዐተ መስቀል ዘዐርብ፤ ብፁዐ አምላክ ጻማዊ ተመሳሌ ቡላ አቢብ፤ ህየንተ ፃማከ ወትዕግሥትከ ዕፁብ፤ ያስተበፅዑከ በሰማይ ትጉሃን አርባብ፡፡ | 22. ለአእዳዊከ፡- አቢብ ቡላን መስለህ የምትደክም ብፁዐ አምላክ ሆይ! ከአብ ምሕረትን ለመለመን በዐርብ መስቀል አምሳል ለተዘረጉ እጆችህ ሰላምታ ይገባል፤ ስለ ድካምህና ዕፁብ ስለሆነ ትዕግሥትህም በሰማይ ያሉ ትጉሃን መላእክት ያመሰግኑሃል፡፡ |
| ፳፫. ሰላም ለመዛርዒከ እለ ጸንዐ ወኀየላ፤ እመዝራዕተ ሶምሶን ምተ ደሊላ፤ ብፁዐ አምላክ ኤልያስ ዘቀጸዖን እግርከ ዕብላ፤ አመ ዐረገ በሠረገላ ኀበ ሉዓላዊት ጌልጌላ፤ ቅድመ ገጸ አምላክ ትቀውም በትፍሥሕት ወተድላ፡፡ | 23. ለመዛርዒከ፡- የእግርህ ጫማ ጨረቃ የሆነልህ ብፁዐ አምላክ ኤልያስ ሆይ! ከደሊላ ባል ከሶምሶን ክንድ ፈጽመው ለበረቱ ክንዶችህ ሰላምታ ይገባል፤ ወደ ከፍተኛይቱ ሰማይ በሠረገላ በሠጠህ ጊዜ በአምላክ ፊት በደስታና በተድላ ትቆማለህ፡፡ |
| ፳፬. ሰላም ለከርናዕከ ጥቅመ ኀጢአት ዘአንኀለ፤ ወመንበረ ሰይጣን ገንጸለ፤ ብፁዐ አምላክ ኪሮስ አምጣነ ተጋደልከ ገድለ፤ ኪያከ | 24. ለከርናዕከ፡- ብፁዐ አምላክ ኪሮስ ሆይ! የኀጢአት ቤትን ለአፈረሰና የሰይጣንን ዙፋን ለገለበጠ ክርንህ ሰላምታ ይገባል፤ ጽኑ ገድልን ስለተጋደልህ አንተን |

| | |
|---|---|
| ዘተውከለ ከመ ኢይርአይ ኀጕለ፤ እግዚአብሔር ሕየው በርእሱ መሐለ። | የታመነ ጥፋትን እንዳያይ እግዚአብሔር በራሱ ማለ፡ ፡ |
| ፳፭. ሰላም ለእመትከ ሕንጸ ተጋድሎ ዘገብረ፤ መቅደሰ ትዕግሥት ግረረ፤ ብፁዐ አምላክ ኀየል እንተ ትገብር መንክረ፤ ኀይለ ጸሎትከ መሥግርተ ጽልመት ሰበረ፤ ወመዛግብቲሃ ለሲኦል በርበረ። | 25. ለእመትከ፡- ድንቅን የምታደርግ ኀያሉ ብፁዐ አምላክ ሆይ! የተጋድሎ ሕንጻ ቦታና የትዕግሥት መቅደስን ለሠራ ክንድህ ሰላምታ ይገባል፤ የጸሎትህ ኀይልም የጨለማን ወጥመድ ሰበረ፤ የሲኦል መዛግብትንም በረበረ። |
| ፳፮. ሰላም ለእራኅቲከ ምንተኒ ዘኢነሥኣ፤ እምንዋየ ዓለም ይግሥሣ፤ ብፁዐ አምላክ ዳዊት ለኢየሩሳሌም ንጉሣ፤ በምጽአትከ ትትፌሣሕ ክኒሳ፤ ወበምጽአትከ ትብል ሐዊሳ ሐዊሳ። | 26. ለእራኅቲከ፡- የኢየሩሳሌም ንጉሥ ብፁዐ አምላክ ዳዊት ሆይ! ምንም ምን ለአልፈለጉና ከዓለም ገንዘብ ለተወገዱ መሐል እጆችህ ሰላምታ ይገባል፤ በአመጣጥህም ቤተ ክርስቲያን ትደሰታለች፤ በአመጣጥህም ሰላም ሰላም ትላለች። |
| ፳፯. ሰላም ለአጻብዒከ መዝሙረ ስብሐት ወውዳሴ፤ እለ ያስተዋድዳ ወትረ ከመ ይሰብሓ ስመ ሥላሴ፤ ብፁዐ አምላክ አቡየ አዕድወኒ ባሕረ ድምሳሴ፤ ወአንብር ዲበ ርእስየ በረከተ እዴከ ሙሴ፤ እስመ ተልሚድከ አነ ወወልድከ አውሴ። | 27. ለአጻብዒከ፡- ብፁዐ አምላክ ሆይ! የሥላሴን ስም የአመሰግኑ ዘንድ የክብርና የምስጋና መዝሙርን ለሚደረድሩ ጣቶችህ ሰላምታ ይገባል፤ አባቴ ብፁዐ አምላክ ሆይ! የጥፋት ባሕርን አሻግረኝ በራሴ ላይም የሙሴ እጅህ በረከትን አስቀምጥ፤ እኔ ተማሪህና ልጅህ ኢያሱ ነኝና። |
| ፳፰. ሰላም ለአጽፋረ እዴከ ከመ ቀጸላ ወርቅ ዘተለብጣ፤ መልዕልተ አጻብዕ የውጣ፤ ብፁዐ አምላክ ዘትቀውም ለባሕረ ማኅው ውሳጤ ውስጣ፤ ለነፍስየ ጸጋማዊት መንገለ የማን ሚጣ፤ ወለኀዘንየ በሐሤት ወልጣ። | 28. ለአጽፋረ እዴከ፡- በጭቃ ባሕር ውስጥ የምትቆም ብፁዐ አምላክ ሆይ! በዐሥሩ ጣቶችህ ላይ እንደ ወርቅ ዘውድ ለተለበጡ የእጅህ ጣቶች ሰላምታ ይገባል፤ በግራ ያለች ነፍሴን ወደ ቀኝ መልሳት፤ ኀዘኔንም በደስታ ለውጥልኝ። |
| ፳፱. ሰላም ለገቦከ አፈ ሦከ ሐፂን ዘቀልጸዎ፤ ወጽንዐ ሕማም ዘአጸንጸዎ፤ ብፁዐ አምላክ ኅሩይ መልከ ጼዴቅ ዘቈላስዎ፤ መኑ ከማከ እምጻድቃን እለ አብዝኁ ፃምዎ፤ ዐሥራተ ምሕረት ዘነሥአ ሲኦለ ጼዊዎ። | 29. ለገቦከ፡- የተመረጠ የቆላስዎ መልከ ጼዴቅ ብፁዐ አምላክ ሆይ! የብረት እሾህ አፍ ለዋጠውና የሕማም ጽናት ለጠመዘዘው ወገብህ ሰላምታ ይገባል፤ ከጻድቃን እንደ አንተ ድካምን የአበዙ እነማን ናቸው! የምሕረት ዐሥራትን ማርኮ ከሲኦልስ ነፍሳትን የተቀበለ ማን ነው! |
| ፴. ሰላም ሰላም ይደሉ በውዳሴ፤ ለመቅደሰ ወንጌል ክርሥከ ዘአኀረመ ቍርባነ ካዕሴ፤ ብፁዐ አምላክ አልዓዛር በቤትከ ቤተ ቅዳሴ፤ አመ ገብሩ ክናሴ አጋዕዝትየ ሥላሴ፤ | 30. ለክርሥከ፡- ብፁዐ አምላክ አልዓዛር ሆይ! የሠንበር ቍርባንን ለተወ ለወንጌል መቅደስ ሆድህ በምስጋና ሰላምታ ይገባል፤ በምስጋና ቤትህ ጌቶቹ ሥላሴ አንድነትን በአደረጉ ጊዜ ሙሴ የአላየውን የምሥጢራት ምሥጢርን አየህ። |

| | |
|---|---|
| ምሥጢረ ምሥጢራት ነፀርከ ዘኢርእየ ሙሴ፡ ፡ | |
| ፴፩. ሰላም ለልብስከ እምነ በቀል ግኑዕ፣ እምጣነ እየር ወየብስ፡ ብፁዐ አምላክ ያሬድ መዘምረ ሥሉስ ቅዱስ፡ ያስተፌሥሕ ኀሊና ሰብእ ማሕሌትከ ሐዲስ፡ ወልበ መላእክት ይመሥጥ ቃልከ ናብሊስ፡፡ | 31. ለልብስከ፡- የሥሉስ ቅዱስ ዘማሪ ብፁዐ አምላክ ያሬድ ሆይ! በአየርና በየብስ መጠን ከበቀል ለራቀ ልብስህ ሰላምታ ይገባል፤ ዐዲስ ምስጋናህም የሰውን ኅሊና ያስደስታል፤ ጸናጽል ቃልህም የመላእክትን ልብ ይመስጣል፡፡ |
| ፴፪. ሰላም ለኵልያቲከ ከመ ለነቢይ ሙሴ ባሕሉ፤ እንተፈተኖን ልዑል ለማኅቶተ ጥበብ በሥነ ጸዳሉ፤ ብፁዐ አምላክ ሚካኤል ለእግዚአብሔር መልአከ ኀይሉ፤ ኀቤከ ይትመሀለሉ እለ ውስተ ሲኦል ኵሉ፤ አውፅአነ አውፅአነ ሠርፀ ጽዮን ይብሉ፡፡ | 32. ለኵልያቲከ፡- የእግዚአብሔር የኀይሉ መልአክ የሆንህ ብፁዐ አምላክ ሚካኤል ሆይ! ልዑል በጥበብ መብራት ብርሃን እንደ ነቢይ ሙሴ ልማድ ለፈተናቸው ኵላሊቶችህ ሰላም ይገባል፤ በሲኦል ያሉ ነፍሳት ኹሉ ወደ አንተ ይማልዳሉ፤ ‹ሠርፀ ጽዮን ሆይ! አውጣን አውጣን› እያሉ ይጮኻሉ፡፡ |
| ፴፫. ሰላም ለኀሊናከ ሐልዮ ትሩፋት ዘእስተሐመመ፤ ኀሊና ሥጋዊ ፍትወት እስመ ፍጹመ አኅረመ፤ ብፁዐ አምላክ ኩነኒ አመ ዕለተ ቅስት ቃውመ፤ ጻድቅ ኀበ አምላኩ ጊዜ ያዜክር ዘጸመ፤ ወሰማዕትኒ ዘከዓወ ደመ፡፡ | 33. ለኀሊናከ፡- የሥጋዊ ፍላጎት ኀሊናን ፈጽሞ ለተወ ለትሩፋት ኀሳብ ለሚተጋ ኀሊናህ ሰላምታ ይገባል፤ ብፁዐ አምላክ ሆይ! ጻድቅ የተጋደለውን የጾመውን ሰማዕትም የአፈሰሰውን ደሞ ወደ አምላኩ በአሳሰበ ጊዜ በፍርድ ቀን አንተ ዋስ ጠበቃ ሁነኝ፡፡ |
| ፴፬. ሰላም ለአማዑቲከ እሳተ ፍቅሩ ዘአልሀቦ፤ ለእግዚአብሔር ፈጣሪ ወአምጻኤ ዓለም እምኀበ አልቦ፤ ብፁዐ አምላክ ግብርከ ዕፁብ ለተናብቦ፤ ለቤልሖር መልአከ ኀጕል አመ ነሠትከ መዝገቦ፤ አዋልዲሃ ለጽዮን የበባ የብቦ፡፡ | 34. ለአማዑቲከ፡- ብፁዐ አምላክ ሆይ! ዓለምን ከአለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረ የእግዚአብሔር የፍቅር እሳት ለአቃጠለው አንጀትህ ሰላምታ ይገባል፤ ሥራህ ለመናገር ድንቅ ነው፤ የጥፋት መልአክ የቤልሖርን መዝገቡን በአጠፋህበት ጊዜ የጽዮን ልጆች ማመስገንን አመሰገኑ፡፡ |
| ፴፭. ሰላም ለንዋየ ውስጥከ ንዋየ ቅድሳት ወንጽሕ፤ ለበግዐ ፍርቃን ክርስቶስ ዘደመ ርግዘቱ ንዙኅ፤ ብፁዐ አምላክ ያዕቆብ ዐርከ ፈጣሪ ምንዙኅ፤ ዜና ኂሩትከ በዝኀ እመሥፈርተ ንባብ ዘኀዙኅ፤ ወተአምሪከ እምኆኖ ብዙኅ፡፡ | 35. ለንዋየ ውስጥከ፡- የፈጣሪ ወዳጅ ብፁዐ አምላክ ያዕቆብ ሆይ! የተወጋውን ደም ለተረጨ ለምስጋና በግ ክርስቶስ የንጽሕና እና የቅድስና ገንዘብ ለሆነ ለውስጥ ዕቃህ ሰላምታ ይገባል፤ ከብዙ ነገር ልክ የደግነትህ ዜና በዛ፤ ተኣምርህም ከምድር አሸዋ ይልቅ የበዛ ነው፡፡ |
| ፴፮. ሰላም ለኀንብርትከ ሠርዌ ቤተ ሥጋ ተመዝባሪ፤ ማእከለ መከየድ ወርእስ ዘአስተዋደዶ ፈጣሪ፤ ብፁዐ አምላክ ሚሳኤል | 36. ለኀንብርትከ፡- የሥቃያት ሸክምን የምትሸከም ብፁዐ አምላክ ሚሳኤል ሆይ! በእግርና በራስ መካከል ፈጣሪ ያስማማውና የፈራሽ ሥጋ ቤት ምሰሶ ለሆነው እምብርትህ ሰላምታ ይገባል፤ አባቴ ሆይ! የቃልህ ፍሬ |

| | |
|---|---|
| ዘበደ ሕማማት በዋሪ፤ ኀጠተ ቃልከ በገራህተ ልብየ ይፍሪ፤ ወንጣውእየ ጽድቅከ ያስተስሪ፤ | በልቤ እርሻ ያፍራ፤ ጽድቅህም ኀጢአቶቼን ያስተስርይልኝ፡፡ |
| ፴፯. ሰላም ለሐቌከ በግብረ ተሐርሞ ቅጡጥ፤ ወበጊጋ ሐጺን ቅጥቁጥ፤ ብፁዐ አምላከ ጳውሎስ ሴታፌ ጴጥሮስ ሥሉጥ፤ ይትከዓው በላዕሌየ መዐዛ እፉከ ቍስጥ፤ ከመ ያእትት ፂዓትየ ዘእፍእ ወውስጥ፡፡ | 37. ለሐቌከ፡- የሥልጣኑ ጴጥሮስ ተባባሪ ብፁዐ አምላክ ጳውሎስ ሆይ! በደም ሥራ ለከሳውና በብረት መንቁር ለተቀጠቀጠው ወገብህ ሰላምታ ይገባል፤ የውስጥና የውጭ የከፋ መዐዛየን ያስወግድልኝ ዘንድ የሽቱ አፍህ መዐዛ በላየ ላይ ይፍሰስ፡፡ |
| ፴፰. ሰላም ለእቍያጺከ አዕማድ ያቁም ወበለዝ፤ እለ ይፀወራ ቦቶን መልክዐተ ኵሉ ትእዛዝ፤ ብፁዐ አምላከ ቁርሎስ መገሥፀ ንስጡር ውጉዝ፤ ገሥፃሙ ለአፅራርየ እኩያነ ምግባር ወግዕዝ፤ እስመ ልማዶሙ ተሀውኮ ወጋዕዝ፡፡ | 38. ለእቍያጺከ፡- የተወገዘ ንስጥሮስን የምትገሥፅ ብፁዐ አምላክ ቁርሎስ ሆይ! የኹሉ ትእዛዝ መልእክቶች ለሚቀመጡባቸው ያቆምና በለዝ ለተባሉ ምሰሶዎች ጭኖችህ ሰላምታ ይገባል፤ ልማዳቸው ሁከትና ጠብ ነውና ሥራቸው እና ጠባያቸው የከፋባቸው ጠላቶቼን ገሥፃቸው፡፡ |
| ፴፱. ሰላም ለአብራኪከ መሥዋዕተ ሰጊድ እለ የዐርጋ፤ ለእግዚአብሔር ፈጣሪ ወገባሬ ኵሎ እንግልጋ፤ ብፁዐ አምላከ ለሲኦል ዘአርኀውከ ቍልፈ መንሡጋ፤ ዔዊወከ ዔዋ አመ ዐረገ በጺጋ፤ መልአከ ሰማይ መሰልከ ዘኢለብሰ ሥጋ፡፡ | 39. ለአብራኪከ፡- የሲኦልን የመዝጊያዋን ቍልፍ የከፈትህ ብፁዐ አምላክ ሆይ! ኹሉን ለፈጠረ ለእግዚአብሔር የስግደት መሥዋዕትን ለሚያሳርጉ ጕልበቶችህ ሰላምታ ይገባል፤ ከሲኦል ምርኮን ማርከህ በጸጋ በወጣህ ጊዜ ሥጋን የለበሰ የሰማይ መልአክን መሰልህ፡፡ |
| ፵. ሰላም ለአእጋሪከ ውስተ ቤተ ጸሎት ወተንብሎ፤ እለ ይቀውማ ወትረ እበለ ጸኒን ወአንቀልቅሎ፤ ብፁዐ አምላክ አቡየ ሐውጸኒ በተሣህሎ፤ ወናዝዝ ኅዘንየ ውስተ ልብየ ዘሀሎ፤ እስመ መምህረ ሕግ አንተ ዘትናዝዝ ኵሎ፡፡ | 40. ለአእጋሪከ፡- ብፁዐ አምላክ ሆይ! በጸሎትና በምልጃ ቤት ያለማዘንበልና ያለመነዋወጥ ዘወትር ለሚቆሙ እግሮጆችህ ሰላምታ ይገባል፤ አባቴ ሆይ! ኹሉን የምታረጋጋ የሕግ መምህር ነህ፤ በይቅርታ ጐብኘኝ፤ በልቤ ውስጥ ከአለው ኀዘኔ አረጋጋኝ፡፡ |
| ፵፩. ሰላም እብል ለሰኳንዊከ መንታ፤ እለ ኢነሰኮን ከይሲ ከመ እግረ ብእሲት ወምታ፤ ብፁዐ አምላክ ሱቱፍ ቅንዋተ መስቀል ዘጎልጎታ፤ ለነፍስየ መሬታዊት አመ የሐልቅ ሕይወታ፤ ውስተ ቤተ ነፍስከ ረሲ ለነፍስየ ቤታ፡፡ | 41. ለሰኳንዊከ የጎልጎታ ችንካሮችን የተሳተፍህ ብፁዐ አምላክ ሆይ! እባብ ለአልነደፋቸውና እንደ ባልና ሚስት እግር መንታ ለሆኑ ተረከዞችህ ሰላም እላለሁ፤ ምድራዊት የሆነች ነፍሴ ሕይወቷ በሚያበቃበት ጊዜ የነፍሴን ማደሪያ በነፍስህ ማደሪያ አድርግልኝ፡፡ |

| | |
|---|---|
| ፵፪. ሰላም ለመከየድከ ውስተ ብሔረ በድው እለ ጌግ፡ ግዱፋን መርጌት ይኅሥሥ፡ ብፁዐ አምላክ ኀያል እምነ ኀያላን ስሳ፡ በድምፀ ቃልከ ቃለ መደንግፅ አንበሳ፡ ተሀውከ ወተከውሰ ለሲኦል ከርሣ፡፡ | 42. ለመከየድከ፡- ከስልሳ ብርቱዎች ይልቅ ብርቱ የምትሆን ብፁዐ አምላክ ሆይ! በምድር የተበደሉትን ይፈልጉ ዘንድ በምድረ በዳ ውስጥ ለገሠገሡ እግሮችህ ሰላምታ ይገባል፤ የሚያስፈራ የአንበሳ ቃል በቃልህ ድምፅ የሲኦል ሆድ ታወከ ተንቀሳቀሰ፡፡ |
| ፵፫. ሰላም እብል ለአጻብዒከ ዘአእጋር፤ ወዘዲቤሆን አጽፋር፤ ብፁዐ አምላክ ዘኮንከ ዕረፍተ ስሩሐን እምፃዕር፤ አሰስል እምላዕሌየ ከበደ ኀጢአት ወነውር፤ እስመ አበሳይ በዝኀ እምኆፃ ዘባሕር፡፡ | 43. ለአጻብዒከ፡- በላያቸው ለአሉ ጥፍሮችና ለእግርህ ጣቶች ሰላም እላለሁ፤ የደከሙትን ከጭንቀት የምታሳርፍ አባቴ ብፁዐ አምላክ ሆይ! በደሊ ከባሕር አሸዋ ይልቅ በዝቷልና የኀጢአት የነቀፋ ሸክምን ከእኔ ላይ አውርድልኝ፡፡ |
| ፵፬. ሰላም ለቆምከ አመ ተክለ ገነት ኀሬ፤ ምሉዐ በረከት ፍሬ፤ ብፁዐ አምላክ አሮን ሥርግወ ትዕግሥት ልብሰ ጸዴሬ፤ ያውዕዮሙ ነደ ቃልከ ለደቂቀ ቅንአት ዘቆሬ፤ እስመ ኢመፍትው ይባኡ ቤተከ ድብታሬ፡፡ | 44. ለቆምከ፡- የግምጃ ልብስ ትዕግሥት የተጎናጸፍህ ብፁዐ አምላክ አሮን ሆይ! በረከት ፍሬን ተሞልቶ ለተመረጠ የገነት ተክል ዛፍ ለሆነ ቁመትህ ሰላምታ ይገባል፤ በማደሪያ ድንኳን ይገቡ ዘንድ አግባብ አይደለምና የቆሬ የቅናት ልጆችን የቃልህ እሳት ያንድዳቸው፡፡ |
| ፵፭. ሰላም ሰላም ለመልክዕከ በአኅብሮ፤ በስብሓት ወበዘምሮ፤ ብፁዐ አምላክ ግብርከ ዕፁብ ለተናግሮ፤ መዛግብተ ሲኦል አመ በርበርከ በርብሮ፤ መላእክተ ሰማይ ወምድር አንከሩ አንክሮ፡፡ | 45. ለመልክዕከ፡- ሥራህን ለመናገር ድንቅ የሆነ ብፁዐ አምላክ ሆይ! በአንድነት በምስጋና እና በዝማሬ ለመልክህ ሰላምታ ይገባል፤ የሲኦልን መዛግብት በበረበርህ ጊዜ የሰማይና የምድር መላእክት መደነቅን ተደነቁ፡፡ |
| ፵፮. ሰላም ለጸአተ ነፍስከ በቃለ ስብሐት ወውዳሴ፤ እንዘ የዐውድዋ ዐውደ መላእክተ ገጽ ወቅዳሴ፤ ምድረ ርስተ ጸጋ ዘቦእከ ብፁዐ አምላክ አውሴ፤ ምድረ ርስት ቤተ ነፍስከ ዘሐነፅዋ ሥላሴ፤ ይምርሐኒ ለበዊእ ጸሎትከ ሙሴ፡፡ | 46. ለጸአተ ነፍስከ፡- በክብርና በምስጋና ቃል የምስጋና መላእክት ዐደባባይን እያዞሯት ወደ ጸጋ ምድረ ርስት የገባህ ብፁዐ አምላክ ኢያሱ ሆይ! ለጸአተ ነፍስህ ሰላምታ ይገባል፤ ሥላሴ የሠሯት የነፍስህ ማደሪያ ምድረ ርስት ለመግባት ሙሴ ጸሎትህ ይምራኝ፡፡ |
| ፵፯. ሰላም ለበድነ ሥጋከ በኈረ ድንግል ዘገነዞ፤ በመዐዛ ዕጣን ንጹሕ እንዘ ያምዕዞ፤ ብፁዐ አምላክ ፍንው ለምሕረት ወለናዝዞ፤ መዛግብተ ሲኦል አመ አግዐዝከ አግዕዞ፤ መኰንነ ጽልመት ደንገፀ በዐቢይ ተከዞ፡፡ | 47. ለበድነ ሥጋከ፡- ለይቅርታና ለመረጋጋት የምትላክ ብፁዐ አምላክ ሆይ! በንጹሕ የዕጣን መዐዛ አጥኖ በኈረ ድንግል ለገነዘው የሥጋህ በድን ሰላምታ ይገባል፤ የሲኦል ነፍሳትን ነፃ በአወጣህ ጊዜ የጨለማው ገዥ በታላቅ ኀዘን ደነገጠ፡፡ |

፵፰. ሰላም ለግንዘተ ሥጋከ ለበኵረ ድንግል በእዱ፤ በልብሰ ሐሜለት ንጹሕ ከመ እለ እንጦንስ አልመዱ፤ ብፁዐ አምላክ በጺጋ እለ ኪያከ ወለዱ፤ ቦ በእግር ዲበ ዘባነ ባሕር ዘሐዱ፤ ወቦ በእሳት ማየ ባሕር አንደዱ፡፡

፵፱. ሰላም ለመቃብሪከ ኀበ ሥላሴ አመሩ፤ እንዘ ይብሉ ዝየ ለሥጋከ መካነ ዝኀሩ፤ ብፁዐ አምላክ ክብሪከ ሶበ በልቡና ነጸሩ፤ እንዘ ይብሉ በእንቲአከ እለ ጳውሎስ ነገሩ፤ እምነ ኮከብ ለኮከብ ይኄይስ ክብሩ፡፡

፶. አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይትባረኩ፤ በዲበ ክብርከ ክብረ ዘለለጽባሑ ወሰኩ፤ ብፁዐ አምላክ በለኒ ሶበ ስመከ ጸዋዕኩ፤ ሠመርኩ መንልየከ ወዕሜተከ አብዛኅኩ፤ እስመ አደመኒ ሊተ ንባብከ ዝኩ፡፡ ድርዐ ሃይማኖት ውጹፍ፤ በሠሊዳ ሰማይ ጽሑፍ፤ አሚነ ሥላሴ እምንእሱ ውኩፍ፤ ብፁዐ አምላክ ልሳነ ሰይፍ፡፡

፶፩. ሰላም ለከ ኮለ ደብረ ቢዘን ሐዋዝ፤ እምነ አፈዋት ምዑዝ፤ በላዔ መጻሕፍት ከመ ሐባውዝ፤ ብፁዐ አምላክ ሥናየ ግዕዝ፡፡

፶፪. ሰላም ለከ ዕንቄ ባሕርይ ጸዐዳ፤ ለጥበበ ሰማይ ወልዳ፤ በላዔ መጻሕፍት ዘብሩር ሠሌዳ፤ ብፁዐ አምላክ መፍቀሬ እንግዳ፡፡

፶፫. ሰላም ለከ ዕፀ ተክህኖ ክቡር፤ ውስተ ቤተ መቅደስ ንቡር፤ በከመ አይድዐ በላዔ ጦማር፤ ብፁዐ አምላክ ሠናየ ዝክር፡፡

፶፬. ሰላም ለከ ዕፀ ሊባኖስ አርያም፤ ምጽላለ አዕዋፍ ኦም፤ ዘኢለከፈከ ርስሐተ ዓለም፤ ብፁዐ አምላክ ጥዑመ ስም፡፡

48. ለግንዘተ ሥጋከ፡- ብፁዐ አምላክ ሆይ! በእነ እንጦንስ ልማድ በንጹሕ የግምጃ ልብስ በበኵረ ድንግል እጅ ለተገነዘው የሥጋህ ግንዘት ሰላምታ ይገባል፤ አንተን በጺጋ ከወለዱት በእግር በባሕር ላይ የተጓዙ አሉ፤ የባሕር ውኃም በእሳት የአነደዱ አሉ፡፡

49. ለመቃብሪከ፡- ብፁዐ አምላክ ሆይ! የሥጋህ የመቃብር ቦታ ‹እዚኽ ነው› እያሉ ሥላሴ ወደ አመለከቱበት ቦታ ለሆነ መቃብርህ ሰላምታ ይገባል፤ ክብርህን በልቡና ባዩ ጊዜ እነ ጳውሎስ ‹ኮከብ ከኮከብ ክብሩ ይበልጣል› ብለው ተናገሩ፡፡

50. ብፁዐ አምላክ ሆይ! በክብር ላይ ክብርን በየጠዋቱ የጨመሩልህ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይባረኩ፤ ስምህንም በጠራሁ ጊዜ ‹ማሕሌትህን ወደድሁ ዋጋህን አበዛሁ› በለኝ፤ ይህ ነገርህ ናፍቆኛልና፡፡ የሃይማኖት ቁመቱን የለበሰ በሰማይ ብራና ተጻፈ ከታናሽነቱ ጀምሮ የሥላሴን ሃይማኖት የተቀበለ ብፁዐ አምላክ አንደበቱ ሰይፍ ነው፡፡

51. ሰላም ለከ፡- የአማረ የደብረ ቢዘን እንኮይ፣ ከሽቱዎች ኹሉ ምዑዝ ሽቱ ያለህ፤ መጻሕፍትን እንደ እንጀራ የምትበላ፤ ጠባየ መልካም ብፁዐ አምላክ ሆይ! ሰላምታ ይገባሃል፡፡

52. ሰላም ለከ፡- ነጭ ባሕርይ የተባለ ዕንቍ፣ የሰማይ ጥበብ ልጅ፤ የብራና መጻሕፍትን ያወቅህ፤ እንግዳ ተቀባይ ብፁዐ አምላክ ሆይ! ሰላምታ ይገባሃል፡፡

53. ሰላም ለከ፡- መጽሐፍ ዐዋቂ እንደ ተናገረ በቤተ መቅደስ የተቀመጥህ፤ ስም አጠራርህ የአማረ ብፁዐ አምላክ ሆይ! ሰላምታ ይገባሃል፡፡

54. ሰላም ለከ፡- የዓለምን ኀጢያት ፈጽሞ ያልነካ፣ የወፎች መጠለያ ዛፍ፤ የሊባኖስ አርያም ዕፅ፣ ስምህ የጣፈጠ ብፁዐ አምላክ ሆይ! ሰላምታ ይገባሃል፡፡

፶፭. ሰላም ለከ ሠዋዔ መለኮት ወሬዛ፤ ለነፍስ ትጉኣን ቤዛ፤ አበ መንፈስየ ለትንቢት ሙኀዛ፤ ብፁዐ አምላክ ስቍረ መበዛ፡፡

፶፮. ሰላም ለከ ዳግማይ ሙሴ፤ ግዱፋነ መርዔት ትጉሜ፤ ካህነ ወንጌል ቍሱላነ ነፍስ ፈዋሴ፤ ብፁዐ አምላክ ገብረ ሥላሴ፡፡

፶፯. ሰላም ለከ ወልደ ዕሤይ በጸጋ፤ እንዘ ይብል ታሪክ መርሙታ፤ ለመርገመ ጌባል በአሚን ነሥታ፤ ብፁዐ አምላክ ርግበ ኤፍራታ፡፡

፶፰. ሰላም ለከ ከመ ጴጥሮስ ዓዲ፤ መቃጥነ ወንጌል ዘይወዲ፤ በሰይፈ ሥላሴ ቈናጽለ ሰዳዲ፤ ብፁዐ አምላክ ሐራ እብኖዲ፡፡

፶፱. ሰላም ለከ አያያተ ኦሪት በላዕከ፤ ወሐሊበ ወንጌል ሰተይከ፤ አሚነ ሥላሴ ሰበከ፤ ኢያንተገ ወኢወሰከ፡፡ ለርስዓንየ ሐድሳ፤ ወለቍስልየ ፈውሳ፤ ኀዘነ ልብየ በሐሤት እንፍሳ፤ ብፁዐ አምላክ ሠርጐ ከኒሳ፡፡ መትልወ ሃይማኖት ዝጉብ፤ ወሐሊበ ወንጌል ጽጉብ፤ ወሪደከ ዝየ እምተድባብ፤ በረከተ ወልድ አኮኑ ዕቁብ፤ ባርከኒ አባ በጥዑም ንባብ፡፡

ኦ አምላኪ አቡነ ብፁዐ አምላክ ዕቀበኒ ወአድኅነኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ ሊተ ለገብርከ..... ወትረ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

አቡነ ዘበሰማያት...

✝ ✝ ✝

55. ሰላም ለከ፡- ሰው የሆነ አምላክን የምትሠዋ፣ የትጉኣን ነፍስ ቤዛ የሆንህ፣ የነፍስ አባቴ፣ የትንቢት ጅረት፣ የሽቱ ውኃ ብፁዐ አምላክ ሆይ! ሰላምታ ይገባሃል፡፡

56. ሰላም ለከ፡- ኹለተኛው ሙሴ፣ የጠፉ መንጋዎችን ፈላጊ፣ የወንጌል ካህን፣ የነፍስ ቍስለኞችን ፈዋሽ፣ የሥላሴ አገልጋይ ብፁዐ አምላክ ሆይ! ሰላምታ ይገባሃል፡፡

57. ሰላም ለከ፡- መርገምን አጠፋት እያለ ታሪክ መርሙታ በወገን የእሴይ ልጅ የሚልህ፣ የኤፍራታ ርግብ ብፁዐ አምላክ ሆይ! ሰላምታ ይገባሃል፡፡

58. ሰላም ለከ፡- እንደ ጴጥሮስ ገና የወንጌል መረብን የሚጨምር፣ በሥላሴ ሰይፍ ቀበሮዎችን የሚያባርር፣ የእብኖዲ ወታደር ብፁዐ አምላክ ሆይ! ሰላምታ ይገባሃል፡፡

59. ሰላም ለከ፡- የኦሪት መዓርን በላህ፤ የወንጌል ወተትን ጠጣህ፤ የሥላሴን ሃይማኖት ሰበክህ፤ አልጨመርህም አላጐደልህም፡፡ ብፁዐ አምላክ ሆይ! ሽምግልናየን አድሳት፤ ቍስሌንም ፈውስልኝ፤ የልቤንም ኀዘን በደስታ ሙላልኝ፡፡ የተጻፈ ሃይማኖትን የምትከተልና የወንጌልን ወተት የጠገብህ ብፁዐ አምላክ ሆይ! ለልጅ በረከት መስጠት የተጠበቀ ነውና አባቴ ሆይ! ከላይ ወደዚኽ ወርደህ በጣፋጭ ነገር ባርከኝ፡፡

አቤቱ የቅዱስ አቡነ ብፁዐ አምላክ ፈጣሪ ልዑል እግዚአብሔር ሆይ! እኔን ባሪያህን..... ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ዘወትር በየጊዜውና በየሰዓቱ አድነኝ ጠብቀኝም ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

አባታችን ሆይ!...

✝ ✝ ✝